## ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ


## የማህበረሰብ አና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርህርት ክፍል

**በ**

**ብሌን ተስፋዬ**


# "እመጓ ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ አላባዉያን አንፃር"

**ነሀሴ/ 2013 ዓ.ም**

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

በ

ብሌን ተስፋዬ

# "እመጓ ልቦለድ  ከረጅም ልቦለድ  አላባውያን አንፃር "

የጥናቱ አማካሪ

መ/ር ተመስገን ሽታዬ

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለ "ባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ " ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ነሀሴ/ 2013 ዓ.ም

## የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማማከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለው፡፡

የአማካሪው ስም

_______________________________________________

ፊርማ_______________________________________________

ይህ በተማሪ ብሌን ተስፋዬ እመን ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ አላባውያን አንፃር በሚል ርዕስ የተሰራው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት እና ደረጃ ያሟላ እና የቴአትር ጥበባት ት/ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው፡፡

ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል ፡፡

ፈታኝ አንድ _______________________________________________

ፊርማ_______________________________________________

ፈታኝ ሁለት _______________________________________________

ፊርማ_______________________________________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ያደረሰኝ አምላክ ክብርና ምስጋና ይግባው። በመቀጠልም ደግሞ አመስግኜ ለማልጨርሰው ለውድ ባለቤቴ እንዲሁም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል መረጃ በመስጠት ላማከረኝ መምህር ተመስገን ሽታዬ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በ 2008ዓም የታተመዉ እመን ልቦለድ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በ እመን ልቦለድ ዉስጥ ባሉት አላባዉያን ላይ የሚያተኩር ሲሆን በተለይም አላባዉያን ላይ ትንተና አድርጓል፡፡ ጥናቱ በእመን ረጅም ልቦለድ ንድፈ ሃሳብ የተተነተነ ሲሆን በጥናቱ ወቅትም የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ ይህዉም ገላጭ አንደመሆኑ መጠን የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መዛግብት ሲሆን መዛግብት በፅሁፉ ደረጃ ያሉ ለህትመት የበቁ ወይም ያልበቁ ሊሆኑ ይችላሉ:: ያለዉ እንዳወቅ ሙሉ "የምርምር መሠረታዊ መርሆች እና አተገባበር" በሚለዉ መፅሀፉ ዉስጥ ስለ መዛግብት እንዲህ ስል ማብራሪያ የሰጣል:: መዛግብት ተመራማሪዉ ስላለፈዉም ይሁን ወቅታዊ ጉዳዮች መረጃ ለመሠብሰብ ሲነሳ ሊጠቀሙባቸዉ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸዉ:: መዛግብት በፅሁፍ መልክ ቤተ መፅሀፍት ፣ ቤተ መዛግብት ወይም ሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች እንደ ሁኔታዉም ከግለሰቦች ሊገኝ የሚችል የመረጃ ምንጭ ናቸዉ:: በመጨረሻም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የእመን ረጅም ልቦለድ አለባውያንን ተንትኖ ጥናቱን አጠቃሏል፡፡

**ማውጫ**


የአማካሪው ማረጋገጫ.......................................................................................i
ምስጋና .......................................................................................................ii
አጠቃሎ.......................................................................................................iii
ምዕራፍ አንድ ................................................................................................ 1
1. መግቢያ ...................................................................................................... 1
1.2. የጥናቱ አላማ ........................................................................................... 2
1.2.1. የጥናቱ ዋና አላማ .................................................................................2
1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ...............................................................................2
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................................ 2
1.4. የጥናቱ ወሰን............................................................................................ 3
1.5. የጥናቱ ዘዴ.............................................................................................. 3
1.5.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ..........................................................................3
1.5.1.1. መዛግብት............................................................................................ 4
1.6. በጥናቱ ውቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ........................................ 4
1.7. የጥናቱ አወቃቀር ...................................................................................... 4
ምዕራፍ ሁለት ................................................................................................ 5
2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት..................................................................................... 5
2.1.1 የስነፅሁፍ ምንነት...................................................................................5
2.1.2 የስነፅሁፍ አይነት ...................................................................................5
2.2 የልቦለድ ምንነት......................................................................................... 6
2.3 የልቦለድ አይነቶች ...................................................................................... 6
2.3.1 የረጅም ልቦለድ ምንነት............................................................................6
2.3.2 የረጅም ልቦለድ አላባውያን .......................................................................7
2.3.2.1 ገፀባገሕርያት............................................................................................ 7
2.3.2.1.1 የገፀባህሪያት አቀራረፅ ዘዴዎች ............................................................... 8
2.3.2.1.2 የገፀባህሪያት አቀራረብ ዘዴዎች.............................................................. 8
2.3.2.1.2.1 ርቱዕ ወይም ዘርዛሪ አቀራረብ .............................................................. 8
2.3.2.1.2.2 ኢ-ርቱዕ ወይም ተዉኔታዊ አቀራረብ ........................................................ 8
2.3.2.2 መቼት...................................................................................................... 9

2.3.2.2.1አጠቃላይ መቼት ........ 9
2.3.2.2.2 ውስን መቼት ........ 10
2.3.2.3 ጭብጥ ........ 10
2.3.2.4 ትልም ........ 10
2.3.2.5. አንፃር ........ 10
2.3.2.5.1 ሁሉን አወቅ አንፃር ........ 11
2.3.2.5.2 ውሱን ሁሉን አወቅ አንፃር ........ 11
2.3.2.5.3 አንደኛ መደብ አንፃር ........ 11
2.3.2.6 ታሪክ ........ 11
2.3.2.7 ግጭት ........ 12
2.3.2.7.1 የግጭት አይነቶች ........ 12
2.3.2.7.1.1 በሰው እና በሰው መካከል ያለው ግጭት ........ 12
2.3.2.7.1.2 ሰው ከራሱ ጋር ያለው ግጭት ........ 13
2.3.2.7.1.3 ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግጭት ........ 13
2.4 የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት ........ 14
ምዕራፍ ሶስት ........ 16
3.1 የደራሲ አለማየሁ ዋሴ እሸቴ ህይወት ታሪክ ........ 16
3.2 እመጓ ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ........ 17
3.3 የእመጓ ልቦለድ ገጸ ባኅሪያት አሳሳል ትንትና ........ 20
3.3.1 የሲሳይ ........ 20
3.3.2. አባ ብረሃነ መስቀል ........ 20
3.3.3. አባ መረሃ ጻድቅ ........ 21
3.3.4. እማሆይ እሴተ ማሪያም ........ 21
3.3.5. አባ አክሊሉ ........ 21
3.3.6. ዶክተር ሻሮን ሎዉማን ........ 22
3.3.7. አንድሪ ባርነስ ........ 22
3.4 የእመጓ ልቦለድ ጭብጥ ........ 23
3.5 የእመጓ ልቦለድ ግጭት ........ 23
3.5.1 ሰዉ ከሰዉ ጋር ያለዉ ግጭት ........ 24
3.5.2 ሰው ከራሱ ጋር ያለው ግጭት ........ 26

3.6 የእመጓ ልብ ወለድ አንፃር ........ 26
3.6.1 ሁሉን አወቅ አንፃር ........ 27
3.6.2 አንደኛ መደብ አንፃር ........ 27
3.7 የእመጓ ልቦለድ መቼት ........ 28
3.7.1 አጠቃላይ መቼት ........ 28
3.7.2. ውስን መቼት ........ 28
3.8 የእመጓ ልቦለድ ትልም ........ 30
ምዕራፍ አራት ........ 31
4. ማጠቃለያ ........ 31
ዋቢ መፅሐፍት ........ 32

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ስነ-ፅሁፍ ዉበት ባለዉ ቋንቋ ተቀነባብሮ የሚቀርብ የኪነ ጥበብ ስራ ነዉ፡፡ ስነ-ፅሁፍ አፋዊ እና ፅሁፋዊ በመባል በሁለት ይክፍላል፡፡ ደራሲዉ የማይታወቅ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በቃል የሚተላለፍ ስነ-ፅሁፍ ቃላዊ ስነ-ፅሁፍ የምንላችዉ ስነ-ቃል፣ትዉፊት(oral literature) ናቸዉ፡፡ ለዚህም አንቆቅልሽ፣ እንካ ሰላምታ፣የባህላዊ ዘፍኖች፣ግጥም፣የለቅሶ ግጥሞች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ደራሲዉ የሚታወቅ በፅሁፍ የሰፈረ የስነ ፅሁፍ ስራ ፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ ይባላል፡፡ አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ ፣ ተውኔት የፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡አጭር ልቦለድ ከ አስር ሺ ባልበለጠ ቃላት የሚፃፍ ጥቂት ገፀ-ባህሪያት ያሉት መቼቱ ጠባብ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የሚፍፅም፣አንድ ጭብጥ ያለዉ የስነ ፅሁፍ ስራ ነዉ፡፡ ረጅም ልቦለድ ስፋ ያለ ታሪክ እና ብዙ ገፀ-ባህሪያቶች ያሉት ታሪኩ በተለያየ ቦታ እና በተለያየ ጊዜያት ሊፈፀም ይችላል፡፡ ሰፊ እና ዉስብስብ ገፀ-ባህሪያት እንዲሁም ከ ሰማኒያ ሺ ባላነሱ ቃላት ሊፃፍ ይችላል፡፡ስነ-ፅሁፍ ፈጠራ በመሆኑ ልቦለድ አና ኢ-ልቦለድ እመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ኢ-ልቦለድ በተፍፀመዉ ድርጊት ላይ ተመርኩዞ ዉበት ባለዉ ቋንቋ የሚቀርብ ስነ-ፅሁፍ ኢ-ልቦለድ በመባል ይታወቃል፡፡ የተፃፉ ነገሮች ዉበት ሳይኖራቸዉ ስነ-ፅሁፍ ተብለዉ ሊጠሩ አይገባም፡፡ ዜና፣የህይወት ታሪክ፣ መግለጫ፣ ደብዳቤ፣ጥናታዊ ፅሁፍ፣ ማስታወቂያ በሚማርክ ቋንቋ ተዘጋጅተዉ ካልቀረቡ ለኢ-ልቦለድ ስነ-ፅሁፍ ምሳሌነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡እመን የልቦለድ መፀሐፍ በደራሲ አለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ\ር) ተደረሰ፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በ 2008 ዓ.ም የተደረሰዉን የእመን ረጅም ልቦለድ ስምንተኛ እትም መፀሐፍላይ ከ አላባዉያን አንፃር ይተነትናል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

አጥኝዋ በዋናነት ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማጥናት ያነሳሳት ምክንያት "እመን" ልቦለድ መፅሀፍ ዉስጥ ያሉ የአላባዉያንን አንፃር ማለትም ገፀ-ባህሪያቱን ፣ ግጭቱን ፣መቼቱን ፣ጭብጡን፣ አንፃርን ፣ታርኩን ፣ ትልሙን ጨምሮ በምን አይነት እንደተገለፀ እና ሌሎች በዉስጡ ያሉትን ለመቃኘት ይሆናል። በተጨማሪ በእመን ልቦለድ ላይ ክአለባዉያን አሳሳል አንፃር በሚል የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ተሰርቶ ስለማያዉቅ።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናታዊ ፁሑፍ በዉስጡ አብይና ንዑሳን አላማዎችን አካቶ የያዘ ነዉ።

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፁሑፍ ዋና አላማ "እመን" የልቦለድ መፅሀፍ ከረጅም ልቦለድ አላባዉያን በምን አይነት እንደተገለፀ  የሚዳስስ ነዉ።

### 1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ✓ የረጅም ልቦለድ አላባዉያንን ምንነትን  ይገልፃል
- ✓ በእመን ልቦለድ መፅሐፍ ዉስጥ ያሉትን የልቦለድ አላባዉያንን ይገልፃል
- ✓ የ እመን መፀሃፍ ከረጅም ልቦለድ አንፃር መለየት

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ጠቀሜታዎች አሉት።

- ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት ሌሎች በዚህ ርዕስ ተመሳሳይ ይዘት ላላቸዉ ፅሁፎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።
- ስለልቦለድ ምንነት ማሳወቅ
- በእመን ልቦለድ ዉስጥ የልቦለድ አላባዉያን መኖራቸዉን ያስረዳል
- በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለ ባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ አእና ለሌሎች ድግሪ ማሚያነት  ያገለግላል

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በደራሲ አለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ /ር) ተደረሶ በ 2008 ዓ.ም በስምተኛ እትም ለአንባቢ በቀረበዉ "እመን" ረጅም ልቦለድ አላባዉያን ይኸዉም ገፀ ባህርያት ፣ ታሪክ ፣ መቼት ፣ ግጭት ፣ አንፃር ፣ ጭብጥ እና ትልምን መተንተን ላይ ትኩረት ያደርጋል።

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ ከሚባለዉ የጥናት አይነት ይመደባል።  ያለዉ እንዳወቅ  ሙሉ "የምርምር መሠረታዊ መርሆች" በሚለዉ መፅሐፉ ዉስጥ ስለ ገላጭ ምርምር እንዲህ ያትታል።  "ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተዉ አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ  ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርጎ በትረካ መንገድ የሚያቀርብበት ነዉ።"

(2009 ፣21)

### 1.5.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

አጥኚዋ  የጥናታዊ ፅሁፍን  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንዲህ ተገልጿል።

#### 1.5.1.1. መዛግብት

መዛግብት በፅሁፉ ደረጃ ያሉ ለህትመት የበቁ ወይም ያልበቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ያለዉ እንዳወቅ ሙሉ (2009 ፣ 191) ገለፃ ስለ መዛግብት እንዲህ ስል ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ መዛግብት ተመራማሪዉ ስላለፈዉም ይሁን ወቅታዊ ጉዳዮች መረጃ ለመሠብሰብ ሲነሳ ሊጠቀሙባቸዉ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸዉ፡፡ መዛግብት በፅሁፍ መልክ ቤተ መፅሀፍት ፣ ቤተ መዛግብት ወይም ሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች እንደ ሁኔታዉም ከግለሰቦች ሊገኝ የሚችል የመረጃ ምንጭ ናቸዉ፡፡”

## 1.6. በጥናቱ ውቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በምትሰራበት ወቅት በዋናነት የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች፣ያጋዥ መፅሃፎች  እና የጊዜ እጥረት አጋጥሟታል፡፡ ስለሆነም በቂ የሆኑ አጋዥ መፅሃፎችን በማፈላለግ እንዲሁም የሚያስፈልገዉን ጊዜ በትጋት በመስራት ይህንን ጥናታዊ ፁሁፍ ማጠናቀቅ ችላለች፡፡

## 1.7. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች ተከፍሏል፡፡ በምዕራፍ አንድ ላይ መግቢያ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አላማ (የጥናቱ ዋና አላማ እና የጥናቱ ንዑስ አላማ)  የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጣሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦችን ያካትታል፡፡  ምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሀሳብ ትንተናን (ስለ ስነ ፅሁፍ ምንነት) እና የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት  ይይዛል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና፣ ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች ፣ ዋቢ መፅሀፍትን ጨምሮ ያካትታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

ከልቦለድ ባህሪያት አንፃር የሚተገበር እንደመሆኑ መጠን በሚቀራረብ መረጃ ከልቦለድ አኳያ የሚስተዋሉ ነጥቦችን መቃኘት አስፈላጊ ነዉ፡፡

#### 2.1.1 የስነፅሁፍ ምንነት

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣3) ገለፃ ስለ ስነ ፅሁፍ እንዲህ በማለት ያብራራል፡፡ "በቁም ሲታይ ስነ ፅሁፍ የሚለው ቃል በፅሁፍ የተቀረፀውን ብቻ የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ የፅሁፍ ባህል ከመጀመሩ አስቀድሞ ስሜቱን የሚገልፅባቸው ቃላዊ ፈጠራዎች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡አሁንም ቢሆን አሉ ወደፊትም ይኖራሉ፡፡ስለዚህ ስነፅሁፍ ስንል ህልውናቸው በቃል የሆነውን ፈጠራዊ ሀሳብ መግለጫ ቅርፆችንም ጭምር መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡"

#### 2.1.2 የስነፅሁፍ አይነት

እንደ ብርሃኑ ገ/ፃድቅ (2008፣107) ገለፃ ስነፅሁፍ አፋዊ እና ፅሁፋዊ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ደራሲው የማይታወቅ ከትውልድወደ ትዉልድ በቃል የሚተላለፍ ስነቃል፣ትውፊት (oral literature) ተብለው ይጠራሉ፡፡ለዚህም እንቆቅልሽ፣እንካስላንቲያ፣የባህላዊ ዘፈኖች ግጥም ፣ የለቅሶ ግጥሞች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ደራሲው የማይታወቅ በፅሁፍ የሰፈረ የስነፅሁፍ ስራን ፅሁፋዊ ስነፅሁፍ ይባላሉ፡፡ለዚህም አጭርልቦለድ፣ረጅም ልቦለድ፣ተውኔት የፅሁፋዊ ስነፅሁፍ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

## 2.2 የልቦለድ ምንነት

ልቦለድ ማለት የገሃዱ አለም እውነታ የምናይበት ሆኖ ደራሲው ያልተገደበ ነፃነት ስላለው ስሜቱን እና ፍላጎቱን የሚያንፀባርቅበት የስነፅሁፍ ዘርፍ ነው።

እንደ ብርሃኑ ገ/ፃድቅ (2008፣107) ገለፃ ልቦለድ ማለት የገሃድ እውነታ አለም ላይ ተንተርሶ ከአእምሮ እየመነጨ ውበት ባለው ቋንቋ አቀናብሮ የሚዘጋጅ የስነፅሁፍ ዘርፍ ነው።

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2008፣153)" የስነፅሁፍ መሰረታዊውያን" በሚለው መፅሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል።

ልቦለድ በመባል የሚታወቁ የስነፅሁፍ ዘር አያሌ ገፅታዎች አሉት። አይነቶቹም ብዙ ናቸው። ሆኖም ለስራችን አመቺነት ያህል በአጠቃላይ በቂ የሆነ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ አይደለም። ብዙዎች ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ እንደምናስበው ይህ የስነፅሁፍ ዘር በዕርግጥም ዘመናዊ እና በዝርው የሚቀርብ ረጅም የፈጠራ ድርሰት ቅርፅ ነው።

## 2.3 የልቦለድ አይነቶች

ብርሃኑ ገ/ፃድቅ (2008፣107) እንደገለፀዉ ልቦለድ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል እነሱም አጭር ልቦለድ እና ረጅም ልቦለድ ይባላሉ። አጭር ልቦለድ የምንለው በቃላት የተገደቡ ጥቂት ገፀባሕርያት ያላቸው ሲሆኑ ረጅም ልቦለድ ደግሞ በተለያየ ጊዜ እና ቦታ የሚቀርብ ብዙ ገፀባህርያቶችን በዉስጡ የያዘ የልቦለድ አይነት ነው።

### 2.3.1 የረጅም ልቦለድ ምንነት

ረጅም ልቦለድ ማለት በተለያየ ጊዜ እና ቦታዎች የሚቀርብ ብዙ ገፀባሕርያት ያሉት በምክንያትና በውጤት የተጣመሩ ድርጊቶች ያለው በውስጡ የተለያዩ ጭብጦች፣ግጭቶችና ታሪኮች የያዘ የልቦለድ አይነት ነው።

### 2.3.2 የረጅም ልቦለድ አላባውያን

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣154) የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ወይም አላባውያን ተብለው የሚታወቁት ታሪክ፣ትልም፣መቼት፣ግጭት፣ጭብጥ ገፀባሕርያት እና አንፃር ናቸው።እነዚህ ለአጠናን እንዲያመች ተደርገው ተለያይተው ተጠሩ እንጂ በልቦለድ ዉስጥ በተናጥል ወገን ለይተው ለየብቻ የሚገኙ አይደሉም።

#### 2.3.2.1 ገፀባገሕርያት

ገፀባሕርያት ማለት በልቦለድ ወስጥ ደራሲው ከሃሳቡ አመንጭቶ የሚፈጥራቸው ግዑዝ አካላት እንሰሳት፣አእዋፋት የገሃዱ አለም ሰዎችን የሚወክሉ ፍጡሮች ናቸው።

እንደ ፋንታሁን እንግዳ (2009፣25) ገፀባሕርያት በገሀዱ አለም ፍጡራን አካል እና አምሳል ተክተው የሚቀረፅ የልቦለድ፣የተውኔት የተራኪ ግጥም በጥቅሉ የፈጠራ ስራዎች ናቸው። በእውነት እና በተጨባጭ አለማችን ረጅም፣አጭር፣አንካሳ፣ሸበቶ፣መልከ ቀና መልከ ጥፉ ጥቁር፣ነጭ እንዳሉ ሁሉ በልቦለድ አለም እነዚህ ሰዎች ይገኛሉ።

ዘሪሁን አስፋው (2005፣190) እንደገለፀዉ ገፀባሕርያት በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው ባህሪ ተጎናፅፈው፣መጠሪያ ተሰቷቸው የሚንቀሳቀሱ የሚተነፍሱ፣ የሚናገሩ፣የሚበሉ፣የሚጠጡ እንደ እውን አለም ሰዎች የሚኖሩ ፣የሚሞቱ፣የሚርባቸው የሚጠማቸው፣የሚፋቀሩ፣ የሚጣሉ፣ የሚደሰቱ፣የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው።

2.3.2.1.1 የገፀባህሪያት አቀራረፅ ዘዴዎች

አንድ ደራሲ ፅሁፉን ከፃፈ በኋላ በራሱ ፍላጎት ገፀባህሪውን ይሰሩልኛል ብሎ ያመነባቸውን የሚመርጥበት ሂደት የገፀባህሪያት አቀራረፅ እንለዋለን፡፡

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣161) ደራሲው ገፀባህርይ በሚቀርፅበት ጊዜ ምርጫ ያደርጋል፡፡ ከተመለከታቸውም ሰዎች መካከል ለፈለገው አላማ አመቺ ይሆናል ብሎ ያመነባቸውን ወይም ገፀባህሪውን በወል ሊያሳዩ ይችላሉ ያላቸውን የተወሰኑ አካላዊና ህሊናዊ መልኮችን ብቻ መርጦ ይወስዳል፡፡

2.3.2.1.2 የገፀባህሪያት አቀራረብ ዘዴዎች

ዘሪሁን አስፋው" የስነፅሁፍ መሰረታዊውያን" በሚለው መፅሐፍ እንዲህ በማለት በሁለት ከፍሎ ያብራራል፡፡

2.3.2.1.2.1 ርቱዕ ወይም ዘርዛሪ አቀራረብ

ዘሪሁን አስፋው (2005፣167) እንደገለፀዉ ርቱዕ ወይም ዘርዛሪ አቀራረብ ገፀባሕርያትን ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ ያልሆነ የአቀራረብ አይነት ነው፡፡በምናነብበት ጊዜ ገፀባሕርያት ስለምንነታቸው ቶሎ እንድንረዳቸው እና እንድናቃቸው ያደርጋል፡፡

2.3.2.1.2.2 ኢ-ርቱዕ ወይም ተዉኔታዊ አቀራረብ

ዘሪሁን አስፋው (2005፣168) እንደገለፀዉ

ኢ-ርቱዕ ወይም ተውኔታዊ አቀራረብ ገፀባህሪውን በድርጊት ያሳያል፡፡

ከባህሪው አመል፣ንግግር አስተሳሰብ እና አመለካከት ስብዕናውን እና

ከሌሎች ገፀባሕርያት ጋር ያለዉን ግንኙነት መገንዘብ ይቻላል፡፡በእውኑ

አለም የምናያቸው ሰዎች ከንግግራቸው እና ግብራቸውን ለመለየት

እንዲያመች ሁሉም ገፀባሕርያት በኢርቱእ ዘዴ ከቀረቡ መልካቸውም

ስብዕናቸውንም ለማወቅ ገፀባህሪዉ ረጅም ይሁን አጭር፣ጠይም ይሁን

ቀይዳማ፣ቀጭን ይሁን ወፍራም፣ታጋሽ ይሁን ግልፍተኛ፣ቸር ይሁን ንፉግ

በወል መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.3.2.2 መቼት

መቼት ማለት በልቦለድ ዉስጥ ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜዉ ቦታዉ እና መህበራዊ ሁኔታዉን የሚያስረዳ ወይም የሚነግረን ነዉ፡፡

እንደ ፋንታሁን እንግዳ (2009፣11) ገለፃ መቼት የአንድ ተውኔት፣ የልቦለድ ፣ግጥም እና ፊልም ታሪክ የሚከናወንበት ቦታ፣ጊዜ እና ማህበራዊ ዕውነታ ነዉ፡፡

ዘሪሁን አስፋው (2008፣179) እንደ ገለፀዉ መቼት ታሪኩ የተከናወነበት ገፀባሕርያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት የገጠር ወይም የከተማ አካባቢ ብቻም አይደለም አያሌ ነገሮችን ይጨመራል፡፡ከገጠሩ እና ከከተማው ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁነቶች አካቶ በመያዙ ጓዘ ብዙ ነዉ፡፡

ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ"በሚለው መፅሐፍ  እንዲህ በማለት መቼትን በሁለት ከፍሎ አብራርቷል፡፡

### 2.3.2.2.1አጠቃላይ መቼት

አጠቃላይ መቼት የተዉኔቱን አጠቃላይ ጊዜ እና ቦታ የሚያሳየን የመቼት አይነት ነው፡፡

2.3.2.2.2 ውስን መቼት

ውስን መቼት ማለት በልቦለድ ውስጥ የምናገኘው ጥቃቅን ቦታዎች እና ጊዜዎችን የሚያሳየን የመቼት አይነት ነው፡፡

2.3.2.3 ጭብጥ

በአንድ ልቦለድ ዉስጥ የምናገኘው ዋና መልዕክት ወይም ፍሬ ሀሳብ ጭብጥ ይባላል፡፡

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣185) ደራሲው አንድን ሀሳብ ወይም ከአንድ በላይ ታሪኮችን ፈጥሮ ገፀባሕርያቱ በተለያዩ ግንኙነቶች ዉሰጥ አስገብቶ ልቦለድን ሲያዋቅር በአብዛኛው ጊዜ መነሻው ይህ ማዕከላዊ ትኩረት ወይም ጭብጥ ነው፡፡

2.3.2.4 ትልም

ትልም ማለት በልቦለድ ውስጥ ለሚያነሱት ጥያቄዎች በምክንያት እና ውጤት የተሳሰረ የድርጊት ቅደም ተከተል ነው፡፡

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣158) ገለፃ ትልም ማለት በአንድ ልቦለድ ውስጥ ምን? ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ የሚያካትት ወይም ደግሞ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁነቶችን የተደረገበትን ምክንያት እና የሚያስከትሉትን ውጤት ጥብቅ ቁርኝት የያዘ የልቦለድ አካል ነው፡፡

2.3.2.5. አንፃር

አንፃር ማለት በዋናነት ደራሲው ታሪኩን የሚያቀናብርበት የትረካ አቅጣጫ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንፃርን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣190) ገለፃ ትልም ማለት ማንኛውም ልቦለድ በደራሲው እና አንባቢው መሀል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅልን እና አልፎ አልፎ በግልፅ በአብዛኛው ጊዜ ግን

በዉስጥ ታዋቂነት የሚኖር የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚገልፅልን ወይም የሚያቀርብልን ተራኪ አለው፡፡

2.3.2.5.1 ሁሉን አወቅ አንፃር

ዘሪሁን አስፋው (2005፣191) እንደ ገለፀዉ ይህ ለተራኪው ሰፊ ነፃነት የሚሰጥ እና በሶስተኛ መደብ የሚተረክ የትረካ አንፃር ነው፡፡ቃሉ እንደሚያመለክተው ተራኪው በልቦለድ ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉ የገፀባህሪያቱን ማንነት፣ስሜት ሀሳብ፣ምኞትና ፍላጎት በሚገባ ያውቃል

2.3.2.5.2 ውሱን ሁሉን አወቅ አንፃር

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2005፣194) ገለፃ ውሱን ሁሉን አወቅ አንፃር እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር በሶስተኛ መደብ የሚተረክ ሲሆን ተራኪው የሁሉም ገፀባሕርያት ስሜት አስተሳሰብም ሆነ ፍላጎት አያውቅም፡፡ የራሱን ፍልስፍና አስተያየት የመንዛት አቅሙ የተገደበ ነው፡፡

2.3.2.5.3 አንደኛ መደብ አንፃር

እንደ ዘሪሁን አስፋው (2002፣196) ገለፃ እኔ ይህን አየሁ፣ይህን ተመለከትኩ እገሌ የሚባልው ገፀባህርይ ወጣ፣በዚህ ወረደ እገሌ ደሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት እገሌ እና እገሌ ተፋቀሩ፣ ተጣሉ ወይም በራሴ ላይ እንዲህ ያለ ድርጊት ተፈፀመብኝ እያለ የሚተርክበት የአንፃር አይነት ነው፡፡

2.3.2.6 ታሪክ

ታሪክ ማለት የልቦለድ ዋና ክፍል የሚይዝ ሲሆን የተለያዩ አንባቢያንን የሚይዝልን የልቦለድ የጀርባ አጥንት ነው፡፡

እንደ ብርሃኑ ገ/ፃድቅ ገለፃ (2008፣108) ታሪክ በልቦለድ ውስጥ በስፋት ትልቁን ቦታ የሚይዝ ነው።ልቦለድ በምናነብበት ጊዜ ታሪኩ አሳዛኝ ይሁን አስቂኝ ወይም እያስተማረ የሚያዝናና ሊሆን ይችላል። በጊዜ ቅደም ተከተል ሁነቶችን የሚያስረዳን ነው።

### 2.3.2.7 ግጭት

ግጭት ማለት በልቦለድ ዉስጥ የተሳሉ ገፀ_ባህሪያት ሁሉም የራሳቸዉን ኑሮ በሚኖሩበት ጊዜ በአንድ ነገር ላይ አለመግባባት ወይም አለመስማማት ይፈጠራል።በሂህም ምክነት ግጭት ይፈጠራል።

እንደ ዘሪሁን አስፋው ገለፃ (2005፣172) ግጭት በሁለት ተቃራኒ ሀያላት መካከል ሌላውን ለማሸነፍ ሌላውን ለመጣል ወይም አንዱ በልላው ላይ የበላይነት ለማግኘት ሲጥር ሌላው ደግሞ ለማሸነፍ ለመውደቅ ወይም ላለመበለጥ ሲፍጨረጨሩ ይታያል።ግጭት ገፀባሕርያቱ ከገቡበት ፍልሚያ ማጥ ለመውጣት ሲጣጣሩ ሌላ ችግር ሲደነቀርባቸው እንደገና ለማርገብ ሲሞክሩ የሚታይበት አይነተኛ ፍሬ ነው።

#### 2.3.2.7.1 የግጭት አይነቶች

በአንድ ልቦለድ ውስጥ የተለያዩ ግጭቶች አሉት። እነሱም ሰዉ ከሰው ጋር፣ሰው ከራሱ ጋር፣ ሰው ከተፈጥሮ ጋር እና ሰው ከፈጣሪው ጋር በመባል ይከፈላሉ።

##### 2.3.2.7.1.1 በሰው እና በሰው መካከል ያለው ግጭት

ዘሪሁን አስፋው "የስነፅሁፍ መሰረታዊያን"በሚለው መፅሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል።

በሰውና በሰው መካከል የሚፈጠረውና ሰው ከሰው የሚባለው ነው።ይህ ሁለት ሰዎች ባላቸው የእምነት፣የፍላጎት፣የአላማ ወይም የአቋም እንዲሁም የአስተሳሰብና የስብዕና ልዩነት ምክንያት የሚፈጠር ነው። (2005፣175)

### 2.3.2.7.1.2 ሰው ከራሱ ጋር ያለው ግጭት

ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ህሊናዊ ወይም ስነልቦናዊ የሚባለው ግጭት ነው።ይህ አይነቱ ግጭት በአንድ ሰው ውስጥ በሚኖሩ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ ነው። (2005፣175)

### 2.3.2.7.1.3 ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግጭት

ዘሪሁን አስፋው "የስነፅሁፍ መሰረታዊያን"በሚለው መፅሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል።"ሰው ከተፈጥሮ ክስተቶችና ገፅታዎች ጋር የሚጋፈጠው ነው። ሰዎች ለመኖር ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች እና ተግባራት ከተፈጥሮ አካላት ጋር ይገናኛሉ። (2005፣176)

2.4 የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት

አጥኚዋ ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች እንዲህ ተመልክታለች። አጥኚዋ ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች ለማዛመድ ባደረገችው ጥረት በሰላማዊት ወርቁ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናታዊ ፅሁፍ አንድነቱን እንደሚከተለው ተመልክታለች ። ጥናታዊ ፅሁፉ በልቦለድ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን በዉስጡም በአራት ምእራፎች ተዋቅሯል። በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣የጥናቱ ዳራ ፣የጥናቱ አላማ (አብይ አላማ እና ንዑስ አላማ ) የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ መጠነርዕይ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ሲይዝ በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሃሳብ ትንተና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና ሲይዝ በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፊትሔ ሀሳብ፣ዋቢ መፅሃፍትን ያስቀምጣል። በሰላማዊት ወርቁ የተሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ተፈጥሮአዊነት በትኩሳት ልቦለድ አስረጂነት በሚል የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን "እመን ልቦለድ ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር" የሚተነትን ነው።

ረድኤት እሱባለው በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርት ድግሪ ማሟያ ያቀረበችው "ኦሮማይ፣ደራሲው እና ከአድማስ ባሻገር ልቦለዶች የሴት ገፀባህርያት አሳሳል እና ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር" በሚል ጥናታዊ ፅሁፉ ሁለቱም በአራት ምእራፎች የተከፈለ ሲሆን  በልቦለድ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣የጥናቱ ዳራ ፣የጥናቱ አላማ (አብይ አላማ እና ንዑስ አላማ) የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ መጠነርዕይ፣የጥናቱ ዘዴ፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን አጠቃልላል።በምእራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ስራ ቅኝት  በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና እና በመጨረሻዉ ምዕራፍ ማጠቃለያ እና የመፊትሔ ሀሳብ፣ዋቢ መፅሃፍትን ያካትታል። በረድኤት

እሱባለው የተሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ኦሮማይ፣ደራሲው እና ከአድማስ ባሻገር ልቦለዶች የሴት ገፀባህርያት አሳሳል እና ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር የሚተነትን ሲሆን "እመጓ"ልቦለድ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር የሚተነትን ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

## 3.1 የደራሲ አለማየሁ ዋሴ እሸቴ ህይወት ታሪክ

ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ እሸቴ በኢትዮጵያ በደቡብ ጎንደር ተወለዱ። በ1992 እንደ ኢሮፓውያን አቆጣጠር የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በሀሮማያ ዩኒቨርስቲ ከግብርና ኮሌጅ በፎረስትሪ ተቀበሉ። ከተመረቁም ብኋላ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ሚንስትርነ በደን ጥበቃ ባለሙያ ተቀላቀሉ።እንደ አውሮፒያን አቆጣጠር በ1995 ወደ ግብርና ሚኒስትር በማቅናት የኢትዮጵያ የደን ልማት ሀላፊ ሆነዉ ሰሩ። ከ1996-2020 እንደ አዉሮፓውያን አቆጣጠር በምግብና ረሀብ በNGO ውስጥ በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀጥረው ሰሩ።እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2019 የመልሶ ግንባታና ማቋቋም መሥሪያ ቤት በአማራ ክልል የደን ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ በመሆን ሰርተዋል። በ1997 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከስዊድን ዩኒቨርስቲ የማስተርስ ድግሪያቸውን አግኝተዋል። ከዛም በመቀጠል በ2007 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የPhD ድግሪያቸውን ከWageningen University አግኝተዋል። ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የቦርድ አባልና ለብዙ ተማሪዎች የመመረቂያ ፁሑፎች አማካሪ በመሆን ሰርተዋል። ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ ከአካዳሚክ ምርምር ስራቸዉ በተጨማሪ የልቦለድ ፀሃፊ በመሆን ካሳተሟቸዉ ፁሁፎች መካክል “እመጓ፣ዝጎራና መርበብት የተሰኙ የአማሪኛ ልቦለዶችን ፃፈዋል።

3.2 እመጓ ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

እመጓ ረጅም ልብወለድ በደራሲ አለማየሁ ዋሴ እሸቴ ተደርሶ በ2008 ዓ.ም ገበያ ላይ በዋለው በስምንተኛው እትም ላይ ያተኮረ ሲሆን ታሪኩም የሚጀምረው ሲሣይ የተባለው ገፅ ባኀሪ ለንግድ ምክንያት አገር አቆርጦ ወደ ውጭ ሀገር ሲሄድ ነበር። እናም በዛው አጋጣሚ በአንድ ወቀት ጉዞ በሚሄድበት ገዳም ውስጥ ተጽፎ ስላገኛው ጽሁፍ ቀጥኛ ትረጉምና ፍችን ፈልጎ ነበር ።ከቆይታ በኁላ የሄደበትን እና የቃላቱን ትርጉም ወደ ሀገሩ ይዞ ይመለሳል። ከተመለሰ ብኂላ አንድ አባት ከገዳም መልእክት ይልኩለትና ምን እንደተፈጠረ ለመጠየቅ በዛውም የቃሉን ትረጉም ለማወቅ የቃሉም ትረጉም እንድህ ይላል ።"ቅዱስ ቅርስ" ከዛም ይህን ፍንጭ ይዞ ጉዞውን ያደረጋል። የገዳሙአባት ካሁን በፊት ይተዋወቁ ስለነበር ወደ እነሱ የመጡበትን ዋና ኣላማ ነግሯቸው የተለያየ የቤተክረሰቲን ክፍል እና ስለእያንዳንዱ ስዕሎች ትርጉም ካስረዳቸው በኂላ እረሱም የጀመረውን ትግል እሰከ መጨረሻ ድረስ መታገል እንዳለበት እና ዳር መድረስ እንዳለበት ነግረውት የገዳሙን ጉዞ መልስ ሳያገኝለት ወደ መጣበት ሊመለስ ሲል ምንም አይነት ምንጭ ባለማግኘቱ በጣም ተናዶ ስለነበረ የኣባን ጸሎት ጨርሶ መንገዱን አቋርጦ ለመሄድ ሲሞክር አስቀድሞ አልፎበት የነበረውን መንገድ አናሳልፍም ብለውት ሳለ ድንገት ሁለት የቤተ ክርሰቲያን እናቶችን ያገኛል ከዛም አታልፍም ብለውት ብለው እንደከለከሉት ሲነግራቸው እማሆይም የት ፣ወደ ደብረ አሮን ነው ጉዞህ ብለው ጠይቀውት እሱም እዛ እንዳለሆነ ይነግራቸውና ጉዞውን ወደ አድስ አበባ እንደሆነ አስረደቶአቸው እሸ

እንግድኅ እንደዛ ከሆነ ቆለኛዋ እማሆይ ይለፍ ብለዋለል ብለህ ንገራቸው እና መሄድ ትችላለህ ብለው ይሸኙታል ፡፡ እሱም የተላከውን መለዕከት ይነግራቸው እና መንገዱን አቋርጦ ይሄዳል ፡ ፡ እናም ከቆይታ በኋላ ቆለኛዋ እማሆይ ያሉትን ነገር ዕያስታወሰ “ደብረ አሮን” ለምን ሊሉኝ ቻሉ ? እዛ ምን አለ ? የሚል ነገር ከንክኖት ቀጥታ ጉዞውነ ወደ ደብረ አሮን እና ከዛ ለመቆየት የሚያስፈልጉትን የተለያዩ የምግብ አይነቶች ይሸምትና እና ደብረ ኣሮን ናዳ ማሪያም ገዳም ይደርሳል ዕናም ኣንድ አባት ያገኝእና በእንግድነት ተቀብለውት ካስተናገዱት በኋላ የገዳሙን የተለያዩ ጉብኝቶችን አድረጎ ግን በሌላ አቅጣጫ  አንድ ሌላ ገዳም እንዳለ ይነግሩት እና እዛ መሄድ እንደማይችል ነገረውት እናም በጣም አስፈሪ ቦታ እንደሆነ አስረድተውት ይለያያሉ ከመነኩሴዎቹ መካከል የሚያውቃቸው ስለነበሩ እሱም በጣም መጠየቅና መመራመር ስለሚወድ አንድ ቀን እሳቸው ተነሰተው ቅዳሴ በሄዱበት እሱመ ተነስቶ ወደ ተከለከለው አስፈሪ ገዳመም ጉዞውን ያደርጋል  ፡፡ ከብዙ ዉጣውረዶች በኋላ የገዳሙን በር በተለያዩ ሀረጎች ተሸፍኖ ያገኘዋል ፡፡በሩንም በትግል ይከፈትና ወደ ውሰጥ ይገባል ፡፡በስኣቱ ማንም የሚያየው ሰው ስላልነበረ ወደ ውሰጥ በጥልቀት ይገባእና የተለያዩ የብረሃን ምሰሎችን ቀስ በቀስ ይጠጋቸዋል ፡፡ ነገር ግን እሱ የፈለገውን ሊያገኝ አልቻለም ፡፡ከዛም በገዳሙ ሌላ አቅጣጫ ያመራል ፡፡ ተደብቆ ሲመለከት ቂሶች ቆመው እየቀደሱ እና የእጣኑ መዐዛም ለየት ያለ ስሜት ፈጥሮለት እነሱን  ለመቅረብ ይሞክራል ፡፡ እነሱ ጋር ለመድረስ ደግሞ ቢያንስ አራት ሜትር ረቀት ያለው ጉድጉዋድ  ይመለከታል፡፡ እናም እንዴት ማቋረጥ እንዳለበት እያሰበ ድንገት የሰው እግር ኮቴ ይሰማ እና ተደብቆ  መከታተል ጀመረ፡፡ ሑለት አገልጋይዎች ቀጥታ

በእጃቸው ሁለት ቁመት ያላቸው ጣውላ አገጣጥመው  ሲሻገሩ ይመለከታል፡፡ በመቅፅበት የእነሱን እግር ተከትሎ ወደ ዋነው ክፍል ያመራል፡፡ ከዛም ነበር ትለቅ ታምር የተፈጠረው ፡፡ ቅዱሱን የኪዳን  ቅርስ ለመንካት ሲጠጋ ከመቅሰፈት ምን እንደነካው ሳይታወቅ እሱ ከሁለት ቀናት በኂላ እራሱን ጤና ጣቢ ውስጥ ተኝቶ እማሆይ አጠገቡ ቁጭ ብለው ይነቃል፡፡ እናም የተፈጠረውን እያስታወሰ እንድህ እያለ ይገልፀዋል ፡ከጭለማ ክፍል ውስጥ ወጥች በወረቃማ ጥልፍ ያማር ሀምራውይ መጋረጃ በእጀ አጥብቄ ይዤ ከላይ ወደ ታች ከቀኝ ወደ ግራ በፈጥነት ገለጥ ሳደረገው ምንነቱ ያልታወቀ  የብረሃን ጎረፍ ከአስደንጋጭ የመብረቅ ሀይል ጋር ተዳመሮ ወደ ለይ ዓንስቶ ማዶ ካለው የዋሻ ቁጥቁዋጦ ጋር አላተመኝ ሲል ገልፆታል፡፡ ከዛም በኂለ አጠገቡ የነበሩትን እማሆይን ይቅርታ ይጠይቅ እና  ከእንግድህ በዚች ሚስጥራዊ የሆነች ሀገር ቀሪ ዘመኑን ለመኖር ይወስናል፡፡ እናም እምነትን  ባሃይል ማግኘት እንደማይቻል "እንደኔ በሀይልም ይሁን እንደ ዕናንተ በእምነት መቀበል ለሚፈቅዱት ግን እላችኂለሁ" ብሎ ታሪኩን ያጠቃልላል ፡፡

## 3.3 የእመን ልቦለድ ገጸ ባኅሪያት አሳሳል ትንትና

### 3.3.1 የሲሳይ

አካላዊ የገፅ ባህሪያት አሳሳል _ አእድሜዉ ወደ አርባዎቹ የሚጠጋ ፣ መካክልኛ ቁመት ያለዉ

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ዘመናዊ ትምህርት የተማረ የተለያዩ ቋንቋ ዎችን የሚያውቅ በብዙ ጥናቶች ላይ የተመራመረ

የመንግስት ሰራተኛ እና የልጆች ዓባት እንደሆኑ ያሳያል።

አባ መረሃ ጽድቅ እንዲህ ይሉታል ።

"የገዳሙ በረከት ለልጆቸህ እንዲደረሳቸው ይህነ ትወስድላቸዋለህ" ብለው

ፓፓያ ፣ ሙዝ ፣ አቮካዶ፣ ካዝሞራ ተቆረጦ በቅረጫት ተሞልቶ

የተዘጋጀውን አሳዩት።( አለማዬዉ ፣55)

ስነ ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - አስተዋይ ፣ትግስተኛ ግን ደግሞ እንደሰው አለፎ አልፎ ተቆጪ ነገሮችን የሚያገናዝብ እና

የሚመረምር ነው።

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል _ ቸር እና ትሁት የሆነ ሰው

### 3.3.2. አባ ብረሃነ መስቀል

አካለዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - እድሜያቸው ወደ ሰባ (70) የሚሆናቸው አዛውንት ፣ ድምጻቸውም በጣም የሚያምር መሆኑን

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - የቤተክርሲትያን አገልጋይ የሆኑ

ስነ ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - በጣም ቀልጣፋ እና ንቁ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ቸር እና ትሁት

3.3.3. አባ መረሃ ጻድቅ

አካለዊ  የገፅ ባህሪ አሳሳል  - ፈርጠም ያለ  ሰውነት   ያላቸው  ቁመናቸው ያማረ

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል   - የቤተክረስቲያን  አገልጋይ የሆኑ

ስነ  ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል  - ቆፈጣና የሆኑ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል- የተረጋጉ ለነገሮች የማይቸኩሉ አገልጋይ ናቸው (አለማዬዉ፣ 48)

3.3.4. እማሆይ እሴተ ማሪያም

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል   -  የቤተክረሲያቲን  አገልጋይ መነኩሴ

ስነ ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል   - ትአግስተኛ እና አስተዋይ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል    - ትሁት ፣ ለነገሮች  የማይቸኩሉ  የተረጋጉ መነኩሴ

ናቸው ።

3.3.5. አባ አክሊሉ

አካለዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ረዘም ያለ ተክለ ቁመና ያላቸው ፣ ፊታቸዉ ቀይ እና አይናቸው

አካባቢ ቆዳቸው የተሸበሸበ ፣ ጸጉራቸው አልፎ አለፎ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ሉጫ ጥቁር እና

ስስ ከንፈር ያላቸው ። (አለማዬዉ፣132)

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - በቴክኖሎጅ ኢኒስቲቲዩት እና በኬሚካል ምህንድስና  የተመረቁ

የቤተክረሲያቲን  አገልጋይ

ስነ - ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል   - የተረጋጉ ለነገሮቸ የማይቸኩሉ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ንቁ መሆናቸውን ሲሳይ እንድህ ይገልጸዋል ከቤተክሪሰቲያኑ ደረሼ

አጭር ጸሎት ካደረኩ በኋላ ወደ እቃቤት አቅጣጫ ስሄድ አንድ

ንቁ መነኩሴ ጓሳ ከተባለው ሳር ገመድ እየፈተሉ የተወሰኑ ተማሪዎች እዚህም እዛም ቁጭ ብለው ሲቀጽሉ አገኘኒቻ (አለማዬዉ ፣ 127)

3.3.6. ዶክተር ሻሮን ሎዉማን

አካላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - እድሜያቸዉ 58 የሆነ

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል -የተማሩ ሳይንቲስት የብዙሀን ህይወት ባለሙያ እና በካሊፎርኒያ የሳይንስ አካዳሚ ዳሬክተር ናቸዉ።

ስነ-ልቦናዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - አስተዋይ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ንቁና ቀልጠፍ ያሉ

3.3.7. አንድሪ ባርነስ

አካላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል -አድሜያቸዉ 70 አመት የሚሆናቸዉ ረዘም ያለ ቁመት ፡ ፀጉራቸዉ ሙሉ በሙሉ ሀጫበረዳ የሚመስል ግንባራቸዉ እና አይናቸዉ አካባቢ ቆዳቸዉ የተሸበሸበ ናቸዉ

(አለማዬዉ፡ 29)

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - የተማሩና በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት እንግሊዘኛ ለማስተማር የመጡ

ሞራላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - ንቁና ደስተኛ ናቸዉ

3.3.8 ፕ/ር ዴቪድ ራምስፊልድ

አካላዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል -የ72 አመት አዛዉንት ፡ፊታቸዉ ሰፋ ያለ ጉንጫቸዉ ስር ትልቅ

ጭምድድ ያለ ኩልኩልት ያላቸዉ የራሳቸዉ ፀጉር ወደ ኋላ ያስተኙ

ማህበራዊ የገፅ ባህሪ አሳሳል - የተማሩ በሀዋርድ ዩንቨርስቲ የተመረቁ የነገረ መለኮት

ትምህርት ያጠኑ ፕሮፌሰር እና አንባቢ

ሞራላዊ -ንቁና ትሁት የሆኑ

## 3.4 የእመጓ ልቦለድ ጭብጥ

ረጅም ልቦለድ የሚገለፅባቸዉ ባህሪያትን ተከትሎ በአንድ ረጅም ልቦለድ ዉስጥ የሚተላለፈዉ ጭብጥ አንድ ብቻ መሆን እንደሌለበት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም እመጓ ልቦለድ ይህን ያማከለ መሆኑን እንደሚከተለዉ ቃኝታለቸ

በእመጓ ልቦለድ ዉስጥ ሊተላለፍ የፈለገዉ መልዕክት እንደ አብይጭብጥ የሰዉ ልጅ ምን ያህል ፅናት እንዳለዉ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ብንዑሳን ጭብጥ ስር ደግሞ ሰወች የተለያየ እምነት ቢኖራቸዉም አምኖ መቀበልን እንጅ በፍፁም ምንም አይነት ጥርጣሬ ሳይኖራቸዉ አምነዉ መቀበል አንዳለባቸዉ ያስረዳል፡፡

> "እንደኔ በሀይልም ይሁን እንደ እናንተ በእምነት መቀበል ለሚፈቅዱት ግን
>
> እልችሏለሁ"፡፡ (አለማዬዉ:205)

## 3.5 የእመጓ ልቦለድ ግጭት

ግጭት በረጅም ልቦለድ ዉስጥ የሚገኝባቸዉ ባህሪያት በአጭር ልቦለድ ዉስጥም ከሚገኙበት ይለያያል፡፡ ይህም ማለት የረጅም ልቦለድ መገለጫ ባህሪያት የሆነዉ ግጭቱ ቅርንጫፍ እያበጀ እየተወሳሰበ መሄድ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

### 3.5.1 ሰዉ ከሰዉ ጋር ያለዉ ግጭት

ሲሳይ ከአካባቢዉ የሚኖር አንድ ገበሬ ጋር የሚያደርገዉ ግጭት

"እንደምን አደርክ የገዳም ቆይታየን ጨርሸ እየተመለስኩ ነዉ ያዉ ላስቸግርክነዉ። አቋርጬ ማለፍ አለብኝ" አልኩት

"አይ ! በሰላዉ ይበላሽብኛል" ሲል ምንድነዉ የምትለዉ ፤ ወይ ትላንት አላሳልፍም ብትል ጥሩ ነበር ፤ አሁን

መኪንዉን እዚህ ጥየ እድሄድ ነዉ የምትፈልገዉ?!" አልኩት (አለማዮዉ፤57)

ሲሳይ ከአባ ጋር የሚያደርገዉ ግጭት

"እባከዎ አባቴያረፈበትን ቦታ ይዉሰዱኝ ወይም ቦታዉን እንዳዉቅ ያግዙኝ"

"ያንን እንኳን ላደርግ አልችልም"

" ለምን ?"

"ስለማይቻል ነዉ ልጄ አትጠይቀኝ አትቀየመኝ"

"ለምን አልቀየምም ? ከመቀየምም በላይ አዝንበዎታለሁ እንጅ ! ተረጋግቸ የምኖረዉን ሰዉ ጉጉት በሚፈጥር ግራ አማሪኛ የእርሰዎ ባልንጀሮች በሆኑ አባቶች ተጠራዉ። ምንም ቢሆን የገዳሙ አባቶች ናቸዉ ብዬ አክብሬ ሄድኩ ።ያገኘሁት ግን ትንሽ ፍንጭ እየተሰጠሁ በሚስጢር ቁልፍ ፍለጋ መዳከር ነዉ ።ከጎጃም እስከ ወሎ ተንከራተትኩ።አሁን ደግሞ ሸዋ መጣሁ ። በመሀል ትርጉም ፍለጋ አሜሪካ ድረስ ሄድኩ ። ምናልባት እንዳውቅ ፈልጋችሁ ከሆነ በግልፅ ቢነግሩን ቅኝት ከሆነው ኑሮዬ ብመለስ " አልኳቸው መረር ብዬ።

“እውነት ነው በረከትን በእምነት እንድትቀበል ወዲህም የትውልዱን ህመም እንድታውቅ ነው፡፡ አንተ ደግሞ ሁሉንም የማወቅ ጉጉት እና ወረት የሚንጠው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና ትጠራና ትማር ዘንድ ይገባ ነበር አሉኝ፡፡”

“ፍላጎታቸሁ ትምህርት መስጠት ከሆነ ታዲያ ይህን ያክል ሚስጥራዊ ማድረግ ለምን አስፈለገ? ሁሉንም ነገር ትውልድ ቢያውቅም ምን አለ? ታሪኩን ምስጥር ፣ መድህኒቱ ምስጥር ፣ ቅርሱ ሁሉም ሚስጥር ማድረግ ምን ይጠቅማል?! እኛስ የክረስቶስ ፍቅር የለን? የቃልኪዳኑ በረከት አይገባንም ?

“አየህ”

“ስማህ !“ አሉ አባ በጣም ከመናደዳቸው የተነሳ እንዲህ አሉ በቁጣ !

“በአፍላ ትጀምራላችሁ በወረት ትተውታላችሁ፡፡ ያወቃችሁትን ትረሳላችሁ ያላወቃችሁትን ለማወቅ ትጥራላችሁ ፤ የያዛችሁትን ትረግጣላችሁ ፤ የረገጣችሁትን ትይዛላችሁ፡፡ ምኞታችሁ ልክ የለውም ፤ አምሮታችሁ ብዙ ነው ፡፡ የአማራችሁን ስታገኙ ወድያው ይሰለቻችኋል፡፡ ተው የተባላችሁትን ትሽራላችሁ፤ የተከለከላችሁትን ትደፍራላችሁ የተፈቀደላችሁን ችላ ትላላችሁ፡፡ ቤተ መቅደስ እንዳትገቡ ብትባሉ ወደ ፊት ቤተመቅደሱን በመስታዎት ሰርታችሁ መቅደሱ ባትገቡ እንኳን ወደፊት ከውጪ ሆናችሁ ማየት ትፈልጋላችሁ፡፡ ሁሉን ማወቅ ትፈልጋላችሁ፡፡ በአንዱም ግን አትጠቀሙም፡፡ ሁሉመ አላችሁ ግን ባዷችሁን ናችሁ ፡፡ ሀይማኖት እንጂ እምነት የላችሁም !” ቀጠሉ አባ ሰውነታቸው እንደ ቅኔ ዘራፊ በስሜት ይናወጣል፡፡ (አለማዬዉ ፤ 162 — 163)

### 3.5.2 ሰው ከራሱ ጋር ያለው ግጭት

እመን ልቦለድ ከአላባዉያን ዉስጥ ግጭትን ያሚላ ሲሆን ሰዉ ከራሱ ጋር ያለዉን ግጭት እንደሚከተለዉ ቃኝታለች።

ሲሳይ ከራሱ ጋር የሚያደርገዉ ግጭት

"አሁን ኢንተርኔት ባይኖር ሊያስቀሩኝ?! እንደው ይህ ኮምፒዉተር የሚባል የፍጥነቱን ያክል እጅግ ቀሽም ነው።" ነገሩ ኮምፒዉተር ምን አደረገ? በቃ ይሄ የሰለጠነው አለም ከቴክኖሎጂው ጋር ከነ አሰራር ድክመቱ እኛም ጋር ሰተት ብሎ ገባ በማለት ነው። (አለማዬዉ ፤7)

በተጨማሪ ደግሞ ከገዳም ተልኮለት የነበረው መልክት ታመሀል የሚል ስለነበር እንዲህ በማለት ገልፆታል።

"ታመሀል ማለት ምንድ ነው?"

በወጣትነት ዘመኔ ከ16 -22 አመቴ ከፍተኛ የሆነ የህክምና ስቃይ ደርሶብኛል። በዚህ ምክኒያት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ሙሉ በሙሉ አቋርጬ ነበር። ነገር ግን ተገቢውን ህክምና ባለማድረጌ ብዙ የስነ ልቦና ጫናዎችንም አሳልፊያለሁ "ታመሀል" ብሎ መልክት መላክ ምን ይባላል? ። (አለማዬዉ ፤39)

"ታመሀል የሚሉኝ ነገር ለዚህ እንዲህ የተሸበርኩ  "ሞተሀል" ቢሉኝ እንዴት ልትሆን ነው እያሉ በእኔ ውስጥ ሁለት ሀሳቦች ጦርነት ያካሂዱብኝ ጀመር። (አለማዬዉ ፤4)

## 3.6 የእመን ልብ ወለድ አንፃር

በእመን ረጅረም ልብ ወለድ በውጥ  አንፃር በሚገባ መቃኘት ቸሉዋል።

3.6.1 ሁሉን አወቅ አንፃር

በእመን ልብ ወለድ ውስጥ አንዱ ገፀባህሪ የሁሉንም ገፀ ባህሪ ምንነት እና ስሜታቸውን ስለሚያውቀው ሲሳይ እንዲህ ይላል።

"ፈርጠም ያለ አካል ያላቸው ቆፍጣና ቁመናቸው እና አለባበሳቸው ሁዳድ ሲያሳርስ የዋለ የገጠር የመሬት አባት አስመስሏቸዋል።(አለማዬዉ ፣48)

3.6.2 አንደኛ መደብ አንፃር

እመን ረጅም ልብወለድ አንደኛ መደብ ደረጃንም የሚያካትት ሲሆን የትረካውም አቅጣጫ "እኔ" እያለ ዋናውን የታሪክ ባለቤት ሲገልፀዉ እንመለከታለን። ለዚህም ማሳያ እንደሚከተለዉ ቃኝታለች።

"ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ስደርስ ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል አልፎ ነበር ። ከመኪና እንደወረድኩኝ ሻንጣዬን አውርጄ ለእነርሱ በተዘጋጀው ጋሪዎች ላይ አድርጌ እየገፋሁ ወደ ውስጥ በፍጥነት ገሰገስኩ ። ከዚህ በፊት አለም አቀፍ በረራ አድርጌ የማላውቅ እስኪ መስለኝ ድረስ ከነበርኩበት የመቸኮል እና ግራ የመጋባት ስሜት የመለሰኝ "አንትን እኮ ነው ! አትሰማም እንዴ ትኬቱን አሳይ እኮ ነው የምልህ!" የሚል ቁጣ ያዘለ የአንድ ሴኩሪቲ ንግግር ነበር። ከሃሳቤ በፍጥነት ተመልሼና ደንገጥም ብዬ ይቅርታ ጠይቄ ትኬቲን ከፓስፖርቴ ጋር በአንድነት ሰጠሁት።

(አለማዬዉ፣5)

"ምን አይነት ጣጣ ነው!" አልኩና ሁለት እጆቼን ከግንባሬ አንስቼ ራሴን ጭምድድ አድርጌ ይዤ ኮምፒውተሩ ላይ አፈጠጥኩበት። የሆነ አረንጓዴ መብራት ኮምፒውተሩ ቁልፍ ላይ ሲበራ አየሁ። (አለማዬዉ፣25)

## 3.7 የእመን ልቦለድ መቼት

እመን ልቦለድ የረጅም ልቦለድን አፃፃፍን የመቼት ገለፃን በሚገባ ያሟላ ነዉ።

### 3.7.1 አጠቃላይ መቼት

የእመን ልቦለድ አጠቃላይ የጊዜ መቼቱ በ 2008 ዓ.ም ሲሆን አጠቃላይ የቦታዉ መቼት ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡

### 3.7.2. ውስን መቼት

"ውስን ከቦታ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ከዉስን ጊዜ ከምሽቱ 1፡30 እንደ ነበር"። (አለማዬዉ ፣ 5)

"ውስን ከቦታ ከዳላስ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ከተነሳው ከሁለት ሰዓት በረራ በኋላ ከጊዜ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሉዚያና ግዛት፣ ኒው አርሊያንስ ከተማ፣ ኒል አርምስትሮንግ ኢንትርናሽናል ኤርፖርት ውስን ደረስን። (አለማዬዉ፣15)

"ውስን ከቦታ ዋሽንግተን ዲሲ ካረፍኩበት ሆቴል እንግዳ ማረፊያ አካባቢ ጊዜው ልክ 2፡31 ላይ አንድ አዛውንት የሆቴሉን በር አልፈው በአይናቸው ቃኘት አድርገው ወደ እኔ አመለከቱ። (አለማዬዉ፣20)

“ውስን ጊዜው ዕለቱ ሐሙስ በወርሃ ሚያዚያ እንደ ሁልጊዜው ከጥዋቱ 12፡30- 1፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ መግባት ያስደስተኛል፡፡ (አለማዬዉ፣37)

“ውስን ከቦታ በባህርዳር ከተማ ቅዳሜ ጠዋት ከሚያስተምሩበት ደብር ሄጄ ከአገልግሎት በኋላ ጠብቄ አገኘኋቸው፡፡ (አለማዬዉ፣73)

“ውስን ከቦታ ደብረ ብርሃን መንዝ፣ ጌራምድር መሃል ሜዳ ማማ ምድር ዋና ከተማው ሞላሌ፣ ላሎ ምድር ዋና ከተማው ወገሬ እና ገብርኤል ዋና ከተማው ዘምሮ ነበር”፡፡ (አለማዬዉ፣83)

“ውስን ከቦታ ደብረ-ብርሃን ከጊዜ 3፡30 አካባቢ ታህሳስ ወር በመሆኑ የጠዋቱ ቅዝቃዜ አይጣል ነው”፡፡ (እመን፣97)

“ከጊዜ 1989 ዓ.ም በወርሃ ግንቦት፣11፡00 ሰዓት በኋላ ሁሌም እንደማደርገው ወደ ቅድስት ስላሴ በተ-ክርስቲያን ሄድኩ፡፡” (አለማዬዉ፣103)

“ውስን ከቦታ ይገም አርባሀራ ከጊዜ፣ ከቀኑ 10፡00 ላይ የሞላሌ መንገደኞች ከወረዱ በኋላ ይገም ነው የምሄደው ብዬ ተሳፈርኩ፡፡” (አለማዬዉ፣124)

በዚህ ልቦለድ ዉስጥ መህበራዊ ሁኔታዉን በሚገባ ገልፆታል፡፡ ይህም ስንል በወቅቱ የነበረዉን ማህበራዊ ኑሮ እርስበርስ ምን ያህል እንደሚተሳሰቡና እንደሚቻቻሉ አንዱ ላንዱ ያለዉን አክብሮት በሚገባ አሳይቷል፡፡

## 3.8 የእመን ልቦለድ ትልም

አእመን ልቦለድ የረጅም ልቦለድ ባህሪ የጠበቀና ያሳካ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ማለትም ለታሪኩ መፈጠር ያልተወሳሰበ አእና ግልፅ የሆነ የልቦለድ ባህሪ በጠበቀ መልኩ የተጓዘ ነዉ፡፡ የሂህነን ረጅም ልቦለድ ትልም እንደሚከተለዉ ይቀርባል፡፡

ታሪኩ በዋናነት የሚያተኩረው ገፀ ባህሪው ወደ ውጪ ሃገር ሲሄድ ነዉ፡፡ የሄደበትም ምክንያት አንድ ቅዱስ ቅርስ ፍለጋ ነበር፡፡ ከዛም ቅርሱን ፍለጋ የተለያዩ ገዳማትን መጎብኘት ይጀምራል፡፡ ከዛም ከተለያዩ የገዳማት አባቶቸ ጋር ባለመግባባት ይለያያሉ፡፡ምክነያቱም በገዳማቱ የሚያገኛቸዉ አባቶች ምንም አይነት ፍንጭ አልሰጥ እያሉት በመጨረሻም ቦታውን ያገኘዋል፡፡ እናም በድፍረት ወደ ውስጥ ይገባል፡፡ምክነያቱም በዉስጡ ጉጉት ስለነበረበት ሁነቶችን ካጣራ በኂላ አሳቻ ሰዓት ጠብቆ ወደ ዋናው ክፍል ይገባል፡፡ እናም ገብቶ የተሰቀለውን መጋረጃ ይዞ በእጅ ሊገልጥ ሲል የተለየ ክስተት ይከሰታል፡፡ በመቅሰፍት ያለ የሌለ ሃይል ከየት መጣ የማይባል የመብረቅ ጎርፍ ከገዳም ውስጥ አውጥቶ ቋጥኝ ውስጥ እንደከተተው ይናገራል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ

ልቦለድ ማለት የገሃዱ አለም ነፀብራቅ በመሆኑ በስነ-ፅሑፍ ውስጥ ይካተታል፡፡ ስነ-ፅሁፍ ዉበት ባለዉ ቋንቋ ተቀነባብሮ የሚቀርብ የኪነ ጥበብ ስራ ነዉ፡፡ ስነ-ፅሁፍ አፋዊ እና ፅሁፋዊ በመባል በሁለት ይክፍላል፡፡ ደራሲዉ የማይታወቅ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በቃል የሚተላለፍ ስነ-ፅሁፍ ቃላዊ ስነ-ፅሁፍ የምንላችዉ ስነ-ቃል፣ትዉፊት(oral literature) ናቸዉ፡፡ ለዚህም አንቆቅልሽ፣ እንካ ሰላምታ፣የባህላዊ ዘፍኖች፣ግጥም፣የለቅሶ ግጥሞች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ ደራሲዉ የሚታወቅ በፅሁፍ የሰፈረ የስነ ፅሁፍ ስራ ፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ ይባላል፡፡ አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ ፣ ተውኔት የፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡አጭር ልቦለድ ከ አስር ሺ ባልበለጠ ቃላት የሚፃፍ ጥቂት ገፀ-ባህሪያት ያሉት መቼቱ ጠባብ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የሚፍፅም፣አንድ ጭብጥ ያለዉ የስነ ፅሁፍ ስራ ነዉ፡፡ ረጅም ልቦለድ ስፋ ያለ ታሪክ እና ብዙ ገፀ-ባህሪያቶች ያሉት ታሪኩ በተለያየ ቦታ እና በተለያየ ጊዜያት ሊፈፀም ይችላል፡፡ ሰፊ እና ዉስብስብ ገፀ-ባህሪያት እንዲሁም ከ ሰማኒያ ሺ ባላነሱ ቃላት ሊፃፍ ይችላል፡፡ስነ-ፅሁፍ ፈጠራ በመሆኑ ልቦለድ አና ኢ-ልቦለድ እመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ እመን የተሰኘው ረጅም ልቦለድ ከልቦለድ አላባውያን አንጻር ትንታኔ አድርጓል፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥ አለባውያን ይኸውም የልቦለዱ ገፀ ባህሪያት፣ ታሪክ፣ ጭብጡ፣ አንፃሩ፣ግጭቱ፣ ትልሙ እና መቼቱ በልቦለድዉስጥ ተገልፁዋል፡፡

# ዋቢ መፅሐፍት


ብርሃኑ ገ/ፃድቅ። (2008) የአማርኛ አጠቃላይ ቋንቋ። በረከት ሀ/የተ/የግ/ማ።

ያለው እንዳውቅ ሙሉ ። (2009) ። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር።ሊትማን መፅሐፍት።

ዘሪሁን አስፋው። (2005) የስነ-ፅሑፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ በንግድ ማተሚያ ቤት።

ፋንታሁን እንግዳ። (2008) ። የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴዎች። አዲስ አበባአርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት

አለማየሁ ዋሴ እሸቴ። (2008) ። እመን።ቲዜድ ህትመትና ማስታወቂያ።

አለምሸት።(1992)። መሰረታዊ የምርምር ዘገባ አፃፃፍ። አዲስ አበባ የቅድስተ ማሪያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክሊቲ ህትመት።